Ethiopian Journal of Indigenous Knowledge and Applied Sciences
Journal-homepage: https://dbujournals.edu.et ISSN 3006-7308 (online)

*Eth. J. Indig. Know. Appl. Sci.*
Vol. 3, No. 2, 2025, 11-22

# ባህል እና ትምህርት፡- ሥነትምህርታዊ ዲስኩር ትንታኔ በተመረጡ የደብረብርሃን ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

ከበደ ይመር
*[1]Department of Amharic and Literature, College of Social and Humanity Sciences, Debre Birhan University, P.O. Box 445, Debre Birhan, Ethiopia

**አሕጽሮተጥናት**

የዚህ ጥናት ዓላማ በ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር እና የማስተማር መስተጋብር ላይ ከሥነትምህርታዊ ዲስኩር አኳያ ትንተና ማድረግ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት በደብረብርሃን ከተማ በሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ስድስት የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአመቺ የንሞና ዘዴ በመምረጥ በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ በድምፅ እና ምሥል መቅረጫ አማካኝነት የ18 ክፍለጊዜ መረጃ ተሰብስቧል፤ ተቀረጿል፡፡ መረጃው ወደ ምዝግብ መረጃነት ከተቀየረ በኋላም በንግግር ልውውጥ ትንተና ዘዴ መሠረት ተተንትኗል፡፡ የትንተናው ውጤትም የማስተናበሪያ እና የማስተማሪያ ዲስኩሮች የአወቃቀር ሥርዓት የአቃፊ እና የታቃፊ ቅንጅት እንደሆነ አመልክቷል፡፡ ይህም የማስተናበሪያ ዲስኩር አቃፊ ሲሆን የማስተማሪያ ዲስኩር ታቃፊ መሆኑን አሳይቷ፡፡ ነገር ግን የማስተናበሪያ ዲስኩር አቃፊ ሊሆን የሚችለው በእርእሰ ጉዳዩ መቋጫ ላይ ሲከሰት ነው፡፡ ከአገልግሎት አኳያም የማስተናበሪያ ዲስኩር የማስተማሪያ ዲስኩር በተቀላጠፈ መልኩ ይካሄድ ዘንድ እገዛ አደርጓል፡፡ በተጓዳኝ የማስተማሪ ዲስኩር የቋንቋ ትምህርቱ ማቅረቢ ሚዲያ በመሆን አገልግሏል፡፡ ስለዚህ መምህሩ በሚያስተምረው የትምህርት ዓይነት ላይ ያለውን ብቃት ለመገምገም መተኮር ያለበት በማስተማሪያ ዲስኩሩ ላይ ነው፡፡ ነገር ግን በክፍል አመራር ችሎታው ላይ ከሆነ በማስተናበሪያ ዲስኩሩ ላይ መሆን እንዳለበት ይህ ጥናት ይጠቁማል፡፡

**ቁልፍ ቃላት**፡- ትምህርታዊ ዲስኩር፣ የማስተናበሪያ ዲስኩር፣ የማስተማሪያ ዲስኩር፣ የንግግር ልውውጥ

## 1. መግቢያ

የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ በእየጊዜው በሚደረግ ጥናት እየተሻሻለ፣ እየታገዘ እና እየታደሰ ለትውልድ የሚሸጋገር ባህል ነው፡፡ ስለሆነም የማስተማር ባህልን በቅጡ ለመረዳት፣ የዘመኑ የቋንቋ ንድፈሐሳብ ውስብስብ በሆነው የመማሪያ ክፍል ዲስኩር ላይ ጥናት እንዲደረግ ይጋብዛል፡፡ ይሁን እንጂ ቋንቋ እንደ ይዘት እና እንደ ማስተማሪያ መሣሪያ ሆኖ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ድርብ አገልግሎት በመስጠቱ ሳቢያ መስተጋብሩን[1] ከሥነትምህርታዊ ዲስኩር አኳያ ለመተንተን አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች አንዱ እንደሆነ ተደጋግሞ ይገለጻል፡፡ እንደዚህ ያለውን ችግር ለማቃለልም የትምህርቱን ይዘት እና የማስተማሪያ ቋንቋውን ለእየብቻ ለያይቶ መተንተን የሚያስችል ዘዴ መተግበር እንደሚያስፈልግ በመስኩ ምሁራን [3, 4] ዘንድ ይታመናል፡፡

ስለሆነም በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚካሄደውን ሥነትምህርታዊ ዲስኩር በቅጡ ለመተንተን የሚያስችል የመተንተኛ ማሕቀፍ[2] (ንድፈሐሳባዊ እና ሥነዘዴያዊ ፅንሰሐሳብ) ለመቀመር ሲሉ በርካታ የተግባራዊ ሥነልሳን ምሁራን (ለአብነትም [4, 5, 6, 7] ጥናት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጉዳይ ላይ አሁንም ቢሆን የጠራ ግኝት ስለሌለ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ምሁራን በእየ ቋንቋው በጥልቀት ጥናት ይደረግበት ዘንድ ጥናት አድራጊዎችን ያነሣሳሉ፤ ይጋብዛሉ፡፡

---

[1] የመማሪያ ክፍል መስተጋብር፡- በመምህሩና በተማሪዎቹ (እንደዚሁም በራሳቸው በተማሪዎቹ) መካከል የሚደረገውን ትብብራዊ የንግግር፣ የተራና የሚና ልውውጥ ያመለክታል [1,2]፡፡

[2] በግእዝ ቋንቋ "ሐቀፈ" ሲባል "አቀፈ፣ ደገፈ፣ በእጅ ጠምጥሞ ያዘ" (በላይ 1999፡16) የሚል ፍቺ አለው፡፡ በዚህ ጽሑፍ "ማሕቀፍ" ሲባል ፅንሰሐሳባዊ ማቀፊያ መያዣያ ለማለት ነው፡፡

**Corresponding author:* selamkalyimer@gmail.com
Received: Mar 15/2025, Revised: June 1/2025, Accepted: Jun 10/2025, Published: Jul1/2025

**ሥነትምህርታዊ ዲስኩር፡-** በዚህ ጥናት በ[5] የቀረበውን ሥነትምህርታዊ ዲስኩር[3] ባጭሩ ለመከለስ እና እንደ ፅንሰሐሳባዊ ማሕቀፍ ለመገልገል ተሞክሯል፡፡ ምክንያቱም ይህ ንድፈሐሳብ ውስብስብነት የሚታይበትን የመማሪያ ክፍል ዲስኩር በተመለከተ ለመተንተን የሚያግዙ ፍንጮችን ጠቁሟል [8]፡፡ ሥነትምህርታዊ ዲስኩር ሲባልም ‘‘በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመምህሩና በተማሪዎቹ መካከል የሚካሄደውን የመማርና የማስተማር ክንውን የሚያመለክት የዲስኩር ዓይነት ነው” [9]፡፡ ሥነትምህርታዊ ዲስኩር የሕጎች ስብስብ እንደሆነ ይናገራሉ[10]፡፡ ሕጎቹም የትምህርቱ ይዘት ሲመረጥ፣ ተከታታይነቱ እና የሚሰጥበት ጊዜ ሲወሰን ተግባራዊ ይደረጋሉ [8]፡፡ ሥነትምህርታዊ ዲስኩር ከሌሎች የዲስኩር ዓይነቶች በሚከናወንበት ዓውድ፣ በተሳታፊዎቹ ማኅበራዊ ሚና እና በዓላማው ይለያል [5]፡፡ የሥነትምህርታዊ ዲስኩር ንድፈሐሳብ በመምህሩና በተማሪው መካከል የሚፈጠረው ግንኙነት መሠረታዊ ምክንያቱ ምንድን ነው? በመማሪያ ክፍል ውስጥ ምን ዓይነት ይዘት ይተላለፋል? ይዘቱ የሚተላለፈውስ በምን መንገድ ነው? በሚሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ያተኩራል [5]፡፡ በሌላ አገላለጽ፣ ሥነትምህርታዊ ዲስኩር በመማሪያ ክፍል የሚሰጠውን ትምህርት የአወቃቀር እና የቅደም ተከተል ሥርዓት እንደሚገልጽ [6] ያስረዳሉ። ይህም የተሳታፊዎቹን ማንነት ከእነ ተግባራቸው አዛምዶ ለመግለጽም ያስችላል።

የሥነትምህርታዊ ዲስኩር ተግባር [6] እንደሚያስረዱት፣ አንድን ነገር በሚፈለገው መንገድ ማስተላለፍ ነው፡፡ በዚህ የዲስኩር ዓይነት የሚተላለፈው ዓቢይ ጉዳይ “ባህል” እንደሆነ [6] ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቱም ባህል ጠቃሚው አብነት እንዲቀጥል፣ ተጨማሪ አዲስ እንዲፈጠር የሚያደርግ ማኅበራዊ እሴት ነው፡፡ በዚህ ሂደት በባህል አስተላላፊውና በባህል ተቀባዩ (በመማሪያ ክፍል ዓውድ በመምህሩና በተማሪው) መካከል ማኅበራዊ ግንኙነት ይፈጠራል፡፡ ይህ ማኅበራዊ ግንኙነት በሦስት ሕጎች አማካኝነት ይከናወናል፡፡

**የደረጃ ተዋረድ ሕጎች፡-** የደረጃ ተዋረድ ሕጎች በመማርና በማስተማር ክንውን እንደ ቅድመ ሁኔታ ይቆጠራሉ፡፡ በማናኛውም ሥነትምህርታዊ ግንኙነት መምህሩ መምህርነትን እንደሚሰለጥን ሁሉ ተማሪውም ተማሪነትን ይማራል፡፡ መምህር መሆን በመማሪያ ክፍል የሚኖረውን ማኅበራዊ ስርዓት (order)፣ ፀባይ (character)ና ሁኔታ (manner) ተረድቶ በአግባቡ መተግበርን ያመለክታል [5]፡፡ ተማሪውም በበኩሉ የመማሪያ ክፍሉን ደንብ አክብሮ እንዴት መጠየቅ፣ እንዴት መመለስ፣ ወዘተ. እንዳለበት ይለምዳል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሕጎች መምህሩ ከተማሪው ጋር ተገቢው ሥልተትምህርታዊ ግንኙነት ይኖረው ዘንድ እንደ መርህ በመሆን ያገለግላሉ፡፡

**የተከታታይነት ሕጎች (Sequencial rules):-** የተከታታይነትን ሕግ አስመልክተው [5] ሲያስረዱ፣ ማንኛውም ሥልተ-ትምህርታዊ ግንኙነት የቅድም ተከተል ሕግ ሊኖረው ይገባል፡፡ ምክንያቱም ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ ማቅረብ እና ማስተላለፍ አይቻልም፡፡ ስለሆነም አንዱ ቀድሞ ሌላው ተከትሎ መምጣት አለበት፡፡ ቅደም ተከተል ካለ ደግሞ የተከታታይነት ሕግም ይኖራል፡፡ የማስተማር ክንውንም በዚህ ሥርዓት መሠረት ይከናወናል፡፡

**የመመዘኛ መስፈርት ሕጎች (Criterial rules)፡-** የመመዘኛ መስፈርት ሕግ መወሰንን የሚመለከት ነው፡፡ መስፈርት ሲባልም [10] እንደሚያብራሩት፣ ተማሪው ተግባራዊ እንዲያደርገው የሚጠበቅ ሥራ ነው፡፡ ለምሳሌ ተማሪው በማኅበራዊ ግንኙነቱ ተገቢውን ተግባቦት መፈጸም ወይም አለመፈጸሙን፣ የሚጠበቅበትን ማኅበራዊ ግንኙነት መወጣት መቻሉን ወይም አለመቻሉን፣ በማኅበራዊ መዋቅሩ የሚገባውን ቦታ ማግኘቱን ወይም አለማገኘቱን፣ ተገቢውን ንግግር ወይም ጽሑፍ ማፍለቅ መቻሉን ወይም አለመቻሉን፣ ወዘተ. ለመረዳት ያገለግላሉ። በእርግጥም ዓላማ አስቀምጦ ማስተማር እስካለ ድረስ ዓላማው ከግብ መድረሱን መመዘን የሚያስችሉ መስፈርቶች ያስፈልጋሉ፡፡ ምክንያቱም በሥልተ-ትምህርታዊ ግንኙነት ሂደት በጣም አስፈላጊው ነገር የተማሪውን ብቃት መመዘን ነው፡፡ ምዘና ከሌለ የትምህርቱ ዓላማ መሳካቱም ሆነ አለመሳካቱ ሊታወቅ አይችልም። ተማሪውም ቢሆን ከስሕተቱ የሚማርበትን ዕድል አያገኝም [5, 12]፡፡

ባጭሩ ማንኛውም ሥነትምህርታዊ ግንኙነት የደረጃ ሕጎችን፣ የተከታታይነት ሕጎችንና የመመዘኛ መስፈርት ሕጎችን አካቶ ይይዛል [5]፡፡ እነዚህ ሦስት የግንኙነት ሕጎች በሁለት አበይት ምድቦች ይጠቃለላሉ፡፡ እነሱም የማስተማሪያ[4]

[3] *የሥነትምህርታዊ ዲስኩር ንድፈሐሳብ ቀማሪ በለንደን ዩኒቨርሲቲ በሚገኘው የሥነትምህርት ተቋም ብዙ የምርምር ሥራዎችን ያበረከቱት* [5] *የተባሉት የሶሾሎጂ* ምሁር ነበሩ (11)፡፡

[4] አስተናበረ ሲባል *“አንድን ስብሰባ ወይም ዝግጅት አቀናበረ፣ አዘጋጀ፣ መራ”* (አማርኛ *መዝገበ ቃላት* [16፡ 315)፡፡ *ነገር ግን በዚህ ጥናት* አስተናበረ ሲባል

(Instructional)ና የማስተናበሪያ (Regulative) ዲስኩር በመባል ይታወቃሉ። የሁለቱ ሥነትምህርታዊ ዲስኩሮች ቅንጅትም በአቃፊነትና በታቃፊነት ግንኙነት የሚገለጽ ነው። ይህም የማስተማሪያ ዲስኩር በማስተናበሪያ ዲስኩር እቅፍ ውስጥ ይገኛል [8]።

የማስተናበሪያ ዲስኩር በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚቀርበውን ማኅበራዊ ድርጊት ለማቀላጠፍ ሲባል የሚከናወን ነው። መምህሩ ትዕዛዝ ለመስጠት፣ የክፍሉን ሥርዓት ለማስጠበቅ፣ ተማሪዎቹን ለመምከር፣ ወዘተ. ይገለገልበታል። ለምሳሌ “ምክሬን ትኩረት አልሰጠኸውም”፣ “ማጥናት አለብህ”፣ “የቡድን ሥራ ትምህርቱን ለመረዳት ያግዛችኋል”፣ “ለትምህርቱ ትኩረት ብትሰጥ ኖሮ፣ መልስህ ትክክል ይሆን ነበር” የሚሉት የመምህሩ ዓረፍተንግግሮች እንደ ቅደም ተከተላቸው ታዛዥነትን፣ ግዴታን፣ ትብብርንና ታማኝነትን ለተማሪው ስለሚገልጹ የማስተናበሪያ ዲስኩርን ያመለክታሉ። ምክንያቱም ማኅበራዊ ስርዓት፣ እሴት፣ ግዴታ፣ ተግባቦታዊ ሕጎች፣ ወዘተ. ከማስተናበሪያ ዲስኩር የሚመደቡ ይዘቶች ናቸው [12] ።

በሌላ በኩል የማስተማሪያ ዲስኩር የሚባለው እውቀትንና ክሂልን በተማሪው ዘንድ ለማሥረጽ ተግባራዊ የሚደረግ ነው [5]። ለምሳሌ “የተሳሳተ መልስ ነው”፣ “ትክክኛ መልስ ነው”፣ “የተሟላ መልስ አይደለም” የሚሉት የመምህሩ ዓረፍተንግግሮች[5] የማስተማሪያ ዲስኩርን ያመለክታሉ። ምክንያቱም ዕውቀት፣ ብቃትና ሳይንሳዊ ሂደት የማስተማር ዲስኩር ይዘቶች ናቸው [12]።

ባጭሩ ሥልተ-ትምህርታዊ ዲስኩር የሕጎች ስብስብ ነው። ሕጎቹም የደረጃ ተዋረድ፣ የተከታታይነትና የምዘና መስፈርት ናቸው። እነዚህ ሦስት ሕጎች የማስተናበሪያና የማስተማሪያ ዲስኩር ተብለው በሁለት ምድቦች ይጠቃለላሉ። የማስተናበሪያ ዲስኩር የደረጃ ተዋረድ ሕጎችንና የተከታታይነት ሕጎችን ያካትታል። የማስተማሪያ ዲስኩር የምዘና መስፈርት ሕጎችን ይያዛል። በጠቅላላው ይህ ንድፈሐሳብ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ‘‘ምን ይዘት ይተላለፍል?’’ እና ‘‘እንዴት ባለ ዘዴ ይተላለፍል?’’ በሚሉት ሁለት የዕውቀት ቅርፆች መካከል ልዩነት እንዳለ ያመለክታል። የዚህ ጥናት ንድፈሐሳባዊ ማሕቀፈም ይሄው ስለሆነ የመረጃ ትንተናውም በዚሁ ተቀንብቦ ቀርቧል። ይሁን እንጂ እስካሁን በተደረገው ክለሳ ድርሳን ሥነትምህርታዊ ዲስኩርን በተመለከተ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜያት ምን ዓይነት ባህሪ እንዳለው የተደረገ ጥናት አልተገኘም። ስለሆነም የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የ[5]ን ሥነትምህርታዊ ዲስኩር እንደ ንድፈሐሳባዊ ማሕቀፍ በመጠቀም በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚካሄደው ዲስኩር ላይ ትንተና ማድረግ ነው። ለዚህም ያመች ዘንድ ይህ ጥናት የሚከተሉትን ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎች አንሥቷል። እነሱም (1) በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜያት የማስተናበሪያ ዲስከር ከማስተማሪያ ዲሰስኩር ጋር ያለው መዋቅራዊ ቅጥ አንባር ምን ይመስላል? እና (2) የማስተናበሪያ ዲስኩር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜያት ለምን ለምን አገልግሎት ይተገበራል? የሚሉት ናቸው።

መምህራን ትምህርቱን ለማቀላጠፍ ሲሉ የሚናገሩትን እና የሚያከናውኑትን ንግግር ያመለክታል፡፡

[5] ዓረፍተንግግሮች የሚለው አገላለጽ ”utterance” ለሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የተሰጠ ፍቺ ነው፡፡ ልክ በጽሑፍ ጊዜ ያለውን የሐሳብ ማሳረፊያ ለመግለጽ ዓረፍተነገር እንደሚባል ሁሉ በመናገር ጊዜም እንደዚሁ ዓረፍተንግግር የሚለው አገላለጽ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

## 2. የአጠናን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜያት የሥነትምህርት ዲስኩር አውቃቅር እና አገልግሎት ሥርዓት ምን እንደሚመስል መግለጽ ነው። ይህን ዓላማ ለማሳካትም ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን በመከተል ናሙና ተመርጧል፤ መረጃ ተሰብስቦ ተተንትኗል።

ጥናቱ የተካሄደው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ በሰሜን ሸዋ ዞን፣ በደብረብርሃን ከተማ በሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ነው። በዚህ ከተማ ሦስት የመንግሥት እና አንድ የግል በድምሩ አራት ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። ለመረጃው አስተማማኝነት ሲባል ሁሉም ትምህርት ቤቶች በጠቅላይ የንሞና ዘዴ ተመርጠው በጥናቱ ተካተዋል።

የጥናቱ ተተኳሪዎች በናሙና በተመረጡት ትምህርት ቤቶች የ2007 የትምህርት ዘመን የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና ተማሪዎች ናቸው። ሦስት ወንድ እና ሦስት ሴት በድምሩ ስድስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በጥናቱ ተሳታፊ ለመሆን እና በምስል እና በድምፅ መቅረጫ አማካኝነት መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ ስለሆኑ በስምምነት ተመርጠው የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል። ከመምህራኑ ጋር ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ፣ እያንዳንዱ መምህር ከሚያስተምርባቸው አንዳንድ

መማሪያ ክፍሎች በነሲብ ንሞና ዘዴ ተመርጠው ስድስት የመማሪያ ክፍሎች ምልከታ ተደርጎባቸዋል። የነሲብ ንሞና ዘዴ በጥቅም ላይ የዋለበት ምክንያትም መምህራኑ ቀድምው ለቀረጻ ያዘጋጁት መማሪያ ክፍል ካለ እሱን በናሙናነት ላለማካት ሲባል ነው። ይህም የመረጃውን አስተማማኝነት ከመጠበቅ አኳያ አስተወጽኦ አድርጓል።

በናሙና የተመረጡት መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ገብተው ሲያስትምሩ በሙሉ ክፍለጊዜው ላይ በድምፅ እና በምሥል መቅረጫ አማካኝነት ምልከታ ተደርጓል፤ መረጃው ተቀርጿል። እያንዳንዱ መምህር ለአራት ክፍለጊዜ የተቀረጸ ሲሆን የመጀመሪያው የማለማመጃ ቀረጻ ስለሆነ በትንተናው አልተካተተም። ነገር ግን ሦስቱ ወደ ምዝግብ መረጃ ከተቀየሩ በኋላ በጠቅላላው አስራ ስምንት ክፍለጊዜያት ትንተና ተደርጎባቸዋል። ምክንያቱም ውስብስብ የሆነው ‘‘ሥነትምህርታዊ ዲስኩር እንዴት እንደሚሠራ በተግባር ለማሳየት በተከታታይ ክፍልጊዜያት የሚቀርበውን ትምህርት ለረጅም ጊዜ ማጥናት አስፈላጊ ነው’’ [6:221]።

ትንተና የተደረገባቸውን ክፍለጊዜያት ወደ ምዝግብ መረጃ ለመቀየር የ[13]ን የምዝግብ መረጃ አዘገጃጀት ደንብ ተግባራዊ ተደርጓል። ምክንያቱም ይህ የምዝግብ መረጃ አዘገጃጃት ደንብ የንግግሩን ቃላዊና ቃል አልባ የሆኑ አላባዊያን አሟልቶ ለመግለጽ ያስችላል ተብሎ ስለሚታመን እና ከአሁን በፊት በርካታ ጥናቶች [18፣ 19 እና 20] ስለተገለገሉበት ነው። በምዝግብ መረጃ ዝግጅት እና በትንተና ወቅት አገልግሎት ላይ የዋሉ የጽሑፍ ስምምነት ምልክቶች፣ ምሕጻረቃላትና ቁጥሮች ከ[13: 24-31]፣ ከ[19:] iii-iv እና ከ[20: ii-iv] ተወስደው ለዚህ ጥናት በሚስማማ መልኩ እንደሚከተለው ተዘጋጅተዋል።

| ምልክቶች፣ ምሕጻረቃላት እና ቁጥሮች | ትርጉም |
|---|---|
| 01፣ 02፣ 03፣ … | የንግግር ልውውጡን ቅደም ተከተል ይገልጻል። |
| መ፣ ተ | መምህር፣ ተማሪ የሚሉትን ይገልጻል። |
| ተ1፣ ተ2፣ ተ3፣ … | ተማሪ አንድ፣ ተማሪ ሁለት፣ ወዘተ. ለማለት ነው። |
| ኪኪኪ ሃሃሃ | ሣቅን ይገልጻል። |
| ( ) | በአጥኚው የተሰጠውን ተጨማሪ ማብራሪያ ያመለክታል። |
| (( )) | ዓረፍተንግግር የተነገረበትን ዓውድ ያብራራል። |
| (?) | መድመጥ ያልቻለ ንግግር መኖሩን ያሳያል። |
| -----> | የሚተኮርበትን ዓረፍተንግግር ይጠቁማል። |
| – | ይህ መስመር ከሥሩ የተሠመረበት ዓረፍተንግግር አጽንኦት የተሰጠው ነው። |
| … | ሆን ተብሎ የተተወ ንግግር መኖሩን ያመለክታል። |
| + + | ረዘም ያለ ዝምታ መኖሩን ያሳያል። |

ስለዚህ መረጃው የመናገር ተራን መሠረት በማድረግ ተመዝግቧል። ወደ ምዝግብ መረጃ የተቀየረውን መስተጋብር የንግግር ልውውጥ ትንተናን[6] በመከተል ትንተናው ተደርጓል። አከዋወኑም የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉን የዲስኩር ክፍሎች በመምረጥ እና ለአብነት የሚሆኑትን በመረጃነት በማቅረብ ነው።

በዚህ መንገድ ተለይተው የወጡት ተተንታኝ ምሳሌዎች በጥናቱ ጥያቄዎች መነሻነት በየፈርጃቸው እየገቡ በመናገር ተራ ልውውጥ ሥርዓት መሠረት ተተንትነዋል። በትንተናው የተገኘው ውጤትም በመስኩ ካሉት ንድፈሐሳቦች እና የጥናት ግኝቶች ጋር እየተመሳከረ ተብራርቶ ቀርቧል።

## 3. ውጤት

እያንዳንዱን የምርምር ጥያቄ መሠረት በማድረግ ወደ ዝርዝር ትንታኔ ለመግባት ያመቺ ዘንድ በቅድሚያ የመማሪያ ክፍል ዲስኩርን አጠቃላይ ዓውድ ማስተዋወቅ ተገቢ ነው። ይህም ፈርጀ-ሰፊ በሆነ ቅጥ አንባር[7] ከማስተናበሪያ እና ከማስተማሪ ዲስኩር አንጻር በመተንተን ይሆናል። ምክንያቱም

---

[6] *የንግግር ልውውጥ፡- ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ተሳታፊዎች አንድን ተግባቦታዊ ዓላማ ከግብ ለማድረስ ሲሉ የተናጋሪነትንና የአድማጭነትን ሚና እየተለዋወጡ የሚያከናውኑት ቃላዊና ቃል አልባ መስተጋብር ነው [14]፡፡ በዚህ ጥናት በመምህሩ እና በተማሪዎቹ መካከል ያለውን የንግግር መስተጋብር ያመለክታል፡፡ ከዚህ የተመሠረተ የንግግር ልውውጥ ትንተና ዘዴ ደግሞ የንግግር መስተጋብርን የሚያጠና የዲስኩር ትንተና ክፍል ነው፡፡ ተሳታፊዎቹ በንግግራቸው አማካኝነት የሚያከናውኑትን ድርጊት፣ ባህርይ፣ ወዘተ. ይመረምራል [15]፡፡ በዚህ ጥናት የመተንተኛ ዘዴ በመሆን አገልግሏል፡፡*

[7] *ቅጥ “ስርዓት፣ ደንብ” [16፡201] ማለት ሲሆን በዚህ ጥናት “ቅጥ አንባር” የሚለው ድርብ ቃል አገልግሎት ላይ የዋለው የንግግር ልውውጡ የተከሰተበትን የአወቃቀር ስርዓት ለመግለጽ ነው፡፡*

ፈርጀ-ሰፊ በሆነ ቅጥ አንባር የሚጀመረው ትንተና ፈርጀ-ጠባብ ለሆነው የድርድር ክንውን የመተንተኛ ዓውድ ለመፍጠርና አስቀድሞ ፍንጭ ለመጠቆም ዕድል ስለሚሰጥ ነው።

1. የማስተናበሪያ ዲስከር ከማስተማሪያ ዲሰስኩር ጋር ያለው መዋቅራዊ ቅጥ አንባር ምን ይመስላል?
2. የማስተናበሪያ ዲስኩር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜ ለምን ለምን አገልግሎት ይተገበራል?

የድርድር ክንውን በተፈጥሮው ፈርጀ-ጠባብ ቅጥ አንባር ያለው ስለሆነ የመማሪያ ክፍል ዲስኩርን ፈረጀ-ሰፊ መዋቅርና ዓውድ ጠቅልሎ ለመግለጽ አያስችልም። ስለሆነም የመማሪያ ክፍል ዲስኩሩን ፈርጀ-ሰፊ መዋቅር ለመግለጽ ከሥልተትምህርታዊ ዲስኩር ንድፈሐሳብ አኳያ ትንተና ማድረግና ለዝርዝር ትንታኔው በቅድሚያ ዓወድ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ ተግኝቷል።
ስልተትምህርታዊ ዲስኩር ሲባልም "በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመምህሩና በተማሪዎቹ መካከል የሚካሄደውን የመማርና የማስተማር ክንውን የሚያመለክት የዲስኩር ዓይነት" ነው [9፡ 67]። በዚህ ንድፈሐሳብ እምነት የመማሪያ ክፍል ዲስኩር የማስተ**ናበሪያ**ና የማስተ**ማሪያ** ዲስኩር በመባል በሁለት ይከፈላል። የሁለቱ ዲስኩሮች መዋቅራዊ ግንኙነትም የአቃፊነትና የታቃፊነት ሲሆን የማስተማሪያ ዲስኩር ምንጊዜም በማስተናበሪያ ዲስኩር እቅፍ ውስጥ ይገኛል የሚለውን [8] ንድፈሐሳብ በመማሪያ ክፍል ውስጥ በተግባር ከቀረበው አኳያ እንመልከት።

ምሳሌ 1

01 መ፡ *አማርኛ*፣ *ምዕራፍ ሁለት*፣ *የቃላት ክፍሎች* *((የሚሉትን አርእስት በጥቁር ሰሌዳው ላይ እንደ ቅደም ተከተላቸው ከላይ ወደታች እየጻፉና ከሥራቸው እያሰመሩ ለተማሪዎቹ ተናገሩ። ከዚያም ወደ ተማሪዎቹ እየተመለከቱ))* *እነዚህ የቃላት ክፍሎች ባለፈው የተነጋገርንባቸው ናቸው።* ++ *የቃላት ክፍሎች ስምንት የነበሩት ወደ አምስት የተከፈሉበትን* ++ *አንደኛው መስተዋድድና መስተፃምር የነበረው መስተዋድድ ተብሎ አንድ ላይ ሆኑ ማለት ነው።* ++ *ሁለተኛ ስንመጣ ተውላጠ ስምና ስም የነበረው ምን ይሆናል ማለት ነው? እ-ኧ-ኽ ስም ተባለ። ከዚያም እንደገና ደግሞ የተቀሩት ግስ፣ እ-ኧ-ኽ እንደገና ቅጽል፣ ተውሳከ ግስ እንዳሉ አይተናል።* … *አሁንም እዚያው ውስጥ ነን ያለነው።* ++ *በዚያው መሠረት ከሥሩ ያሉ አንዳንድ ነገሮችን እየሠራን ነው ያለነው።*
(ምዝግብ መረጃ ሀ፣ ከ1)

የማስተናበሪያ ዲስኩር አገልግሎት፣ የማስተማሪያ ዲስኩር በአግባቡ ይከናውን ዘንድ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው። ይህም የመማሪያ ክፍሉን ሥርዓት ማስጠበቅ፣ የተማሪዎቹን ባህሪ ማስተካከል፣ ትምህርቱን አንድ ሁነኛ መልክ አስይዞ ማቅረብ፣ ተማሪዎቹን ለትምህርቱ ዝግጁ ማድረግ፣ ወዘተ. ይሆናል። ስለዚህ ከዚህ በላይ በምሳሌ አንድ ላይ እንደሚታየው፣ አሁን ከተዘረዘሩት ተግባራት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ዓረፍተንግግሮች ከሥራቸው የተሰመረባቸው ናቸው። እነዚህም "አማርኛ፣ ምዕራፍ ሁለት፣ የቃላት ክፍሎች … እነዚህ የቃላት ክፍሎች ባለፈው የተነጋገርንባቸው ናቸው … አሁንም እዚያው ውስጥ ነን ያለነው። ++ በዚያው መሠረት ከሥሩ ያሉ አንዳንድ ነገሮችን እየሠራን ነው ያለነው" የሚሉት ናቸው።
እነዚህ ዓረፍተንግግሮች የማስተናበሪያ ዲስኩርን የሚያመለክቱ ናቸው። ምክንያቱም መምህሩ በጥቁር ሰሌዳው ላይ በቅድሚያ "የቃላት ክፍሎች" ብለው አርእስት ጽፈዋል፤ ተናግረዋልም። የዕለቱ ትምህርት ስለሆነ መምህሩ ለተማሪዎቹ እያስተዋወቁ ነው። በዚህ የተነሣም የተማሪዎቹ ትኩረት በቃላት ክፍሎች ላይ ሆኖ ስለቃላት ክፍሎች ያሰላስላሉ፤ የቃላት ክፍሎችን ለመማርም ዝግጁ ይሆናሉ።
ሌላው የዚህ ዲስኩር መሠረታዊ ቁምነገር፣ ተማሪዎቹ ባለፈው ክፍለጊዜ በተማሩትና አሁን በሚማሩት ትምህርት መካከል ያለውን ዝምድና መግለጽ ነው። ለዚህም "አሁንም እዚያው ውስጥ ነው ያለነው" የሚለው ዓረፍተንግግር ሁነኛ ማስረጃ ነው። ይህም የትምህርቱ ይዘት ከቃላት ክፍሎች እንዳልወጣና ከባለፈው የቀጠለ መሆኑን ያስገነዝባል። በዚህ ሳቢያም ተማሪዎቹ የቀደመዕውቀታቸውን ከአሁኑ ትምህርት ጋር ለማዛመድ ጥረት ያደርጋሉ። በተጨማሪም መምህሩ የመልመጃ አሠራር ብልሃቱ ባለፈው ክፍለጊዜ ከተገለገሉበት ያልተለየ መሆኑን "በዚያው መሠረት ከሥሩ ያሉ አንዳንድ ነገሮችን እየሠራን ነው …" በማለት አስለብመዋል። እነዚህ ከዚህ በላይ የቀረቡት ጥቁምታዎች ወደ ማስተማሪያ ድስኩር ለመግባት መንደርደሪያ በመሆን አገልግለዋል። ምክንያቱም መምህሩ የትምህርቱን

ርእስ አስተዋውቀዋል፤ ባለፈው ክፍለጊዜ ያስተማሩትን ከልሰዋል፤ መልመጃው የሚሠራበትን ብልሃት ጠቁመዋል። ስለሆነም በመማሪያ ክፍል ባህል፣ ተማሪዎቹን ለትምህርቱ ዝግጁ አድርገዋል ተብሎ ይወሰዳል። እንደዚህ ያሉት ክንውኖች የማስተናበሪያ ዲስኩር አገልግሎትን የሚገልጹ ናቸው።

ቀደም ብሎ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ የማስተማሪያ ዲስኩር በማስተናበሪያ ዲስኩር እቅፍ ውስጥ ይገኛል። የማስተማሪያ ዲስኩር የሚባለው ዕውቀትን ለማሥረጽና ክሂልን ለማበልጸግ ተግባራዊ የሚደረግ ነው [5]። ምክንያቱም "ዕውቀት፣ ብቃትና ሳይንሳዊ ሂደት የማስተማር ዲስኩር ይዘቶች ናቸው" [12: 562]። ስለዚህ የማስተማሪያ ዲስኩር፣ ተማሪዎቹ ስለሚማሩት ቋንቋ ዕውቀት፣ ግንዛቤ እና ክሂል ያገኙ ዘንድ ትምህርቱ የሚሰጥበት የቋንቋ አጠቃቀም ስርዓት ነው። ለአብነተም

*++ የቃላት ክፍሎች ስምንት የነበሩት ወደ አምስት የተከፈሉበትን ++ አንደኛው መስተዋድድና መስተፃምር የነበረው መስተዋድድ ተብሎ አንድ ላይ ሆኑ ማለት ነው። ++ ሁለተኛው ስንመጣ ተውላጠ ስምና ስም የነበረው ምን ይሆናል ማለት ነው? እ-ኧ-ኧ ስም ተባለ። ከዚያም እንደገና ደግሞ የተቀሩት ግስ፣ እ-ኧ-ኧ እንደገና ቅጽል፣ ተውሳከ ግስ እንዳሉ አይተናል።*

የሚለው ንግግር የማስተማሪያ ዲስኩርን ያካትታል። ምክንያቱም የመምህሩ ገለጻ ስለቃላት ክፍሎች የሚያስገነዝብ ነው። መምህሩ ስለአማርኛ ቋንቋ የቃላት ክፍሎች ያስተማሩትን ሲከልሱ በጥንታዊ የሰዋስው ጠቢባን በስምንት ተከፍለው ይጠኑ የነበሩት አሁን በዘመናዊ የሰዋስው ምሑራን እንደገና በአምስት መከፈላቸውን እያብራሩ አስረድተዋል። በዚህ መልኩ ግንዛቤ ማስጨበጥ ደግሞ ከማስተማሪያ ዲስኩር አገልግሎት የሚፈረጅ ነው። በእርግጥ የማስተናበሪያ ዲስኩር የሚከሠተው በትምህርቱ መጀመሪያ ላይ ብቻ አይደለም። አንዱ ርእሰጉዳይ አልቆ ሌላው ከመቀጠሉ በፊትም ይቀርባል። ዓላማውም የተጀመረው ርእሰጉዳይ መቋጨቱንና ሌላ ርእሰጉዳይ መጀመሩን በመግለጽ ነው። ስለዚህ የማስተናበሪያ ዲስኩር በመሸጋገሪያነትም ያገለግላል።

ምሳሌ 2

--->118 መ፡ እሺ! <u>ይሄ ግልጽ ከሆነ</u> ከዚህ በታች ሥነቃል በሚል እርእስ የቀረበ አንድ ጽሑፍ አለ። ይህን ጽሑፍ ሰባት ደቂቃ እሰጣችኋለሁ፤ በሰባት ደቂቃ ውስጥ አንብቡና እስኪ ከመልዕክቱ የተረዳችሁትን ትነግሩኛላችሁ። የምታነቡት ግን በለሆሳስ ነው። በግላችሁ፤ ሁላችሁም።

ተ፡ ((በግላችው በአርምሞ እያነበቡ
ነው))

(ምዝግብ መረጃ ለ፣ ክ1)

ከዚህ በላይ ከቀረበው የንግግር ልውውጥ መመልከት እንደሚቻለው በ118ኛው የንግግር ተራ ላይ "… ይህ ግልጽ ከሆነ" የሚለው የመሸጋገሪያ ንግግር የተጀመረው ርእሰጉዳይ መጠናቀቁን ይጠቁመዋል። በዚህም መምህሩ ከተማሪዎቹ በኩል የሚነሣ ቅሬታ ወይም ጥያቄ አለመኖሩን ካረጋገጡ በኋላ ቀጣዩን ርእሰጉዳይ አስተዋውቀዋል። ይህም "… ከዚህ በታች ሥነቃል በሚል ርእስ የቀረበ አንድ ጽሑፍ አለ" የሚል ሲሆን መምህሩ ከአንዱ ርእሰጉዳይ ወደ ሌላው መሸጋገራቸውን ያመለክታል።

በተጨማሪም የማሰተናበሪያ ዲስኩር ተማሪዎቹን ለተሳትፎ ለማነሣሳት ሲባልም በሌላኛው መማሪያ ክፍል ተግባራዊ ተደርጓል። ለአብነትም ከዚህ በታች ከ126 እስከ 131 ያለውን የንግግር ልውውጥ፣ መምህርቷ አንድን ምንባብ ካነበቡ በኋላ ተማሪዎቹ የተረዱትን ይናገሩ ዘንድ ለማነሣሻነት ተገልግለውበታል።

ምሳሌ 3

125 መ፡ የተረዳችሁትን ዋና ዋና ነጥብ እስኪ
ንገሩኝ ^

--->126 ተ፡ ((አንድ ተማሪ እጁን አወጣ))

127 መ:ይሄ ተማሪ ብቻ ነው ያነበበው?

128 ተሀ፡ +

129 መ፡ ሌሎቻችሁስ ^ አላነበባችሁም
እንዴ?

130 ተሀ፡ +

131 መ፡ እሽ ^

(ምዝግብ መረጃ ለ፣ ክ1)

ከዚህ በላይ ከቀረበው የንግግር ልውውጥ ማስተዋል እንደሚቻለው፣ መምህርቷ ቢያነሣሱም ተማሪዎቹ ምላሽ አልሰጡም፤ ዝም ብለዋል። ዝምታውን መነሻ በማድረግ መምህርቷ በ125ኛው

የመናገር ተራ ላይ "የተረዳችሁትን ዋና ዋና ነጥብ እስኪ ንገሩኝ" በማለት በጥያቄው ላይ ማሻሻያ አድርገዋል፡፡ ጥያቄውን ቢያሻሽሉም የጠበቁትን ያህል ተሳታፊ አላገኙም፡፡ ምክንያቱም ለተሳትፎ እጁን ያወጣው አንድ ተማሪ ብቻ ነው፡፡

ስለሆነም መምህርቷ፣ ተማሪዎቹ ማኅበራዊ ኃላፊነት እንዲሰማቸውና የተማሪነት ግዴታቸውን እንዲወጡ ጫና በማድረግ "ይሄ ተማሪ ብቻ ነው ያነበበው?" በማለት ለሦስተኛ ጊዜ አነሣሥተዋል፡፡ በዚህ ጥያቄ አማካኝነትም እጃቸውን ለተሳትፎ ባላወጡት ተማሪዎች ላይ፣ "እኔስ?" ብለው ራሳቸውን እንዲጠይቁ የሥነልቦና ጫና አድርገውባቸዋል፡፡ ስለዚህ የማስተናበሪያ ዲስኩር ተማሪዎቹ የተማሪነት ማኅበራዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ለማድረግም አገልግሏል፡፡ ይሁን እንጂ ተማሪዎች ለተሳትፎ ተጋብዘናል በሚል ሰበብም በዘፈቀደ እንዲናገሩ አይፈቀድላቸውም፡፡ የመናገር ተራውን ለማስፈቀድም ቢሆን በጸጥታ እጃቸውን ማውጣትና የመምህራቸውን ፍቃድ መጠባበቅ አለባቸው፡፡

ምሳሌ 4

| | | |
|---|---|---|
| 168 | ተሀ፡ | እኔ ቲቸር! ቲቸር! |
| 169 | መ፡ | ቆይ! እጃችሁን ዝም ብላችሁ አውጡ! |

(ምዝግብ መረጃ ሐ፣ ክ3)

በዚህ የንግግር ልውውጥ ላይ እንደሚስተዋለው፣ ተማሪዎቹ የመምህርቷን ትኩረት በመሳብ የመናገር ተራውን ለማግኘት "እኔ ቲቸር! ቲቸር!" እያሉ ተሯሯጠዋል፡፡ በእርግጥ ይህ ፉክክር ተማሪዎቹ ለመሳተፍ ያላቸውን ብርቱ ፍላጎት የሚያመለክት ቢሆንም የመማሪያ ክፍሉን ደንብ ያከበረ አይደለም፡፡ በመማሪያ ክፍል ባህል የመናገር ተራውን መቆጣጠርም ሆነ ፍቃድ መስጠት የመምህራን ሥልጣን ስለሆነ የመናገር ዕድል አልሰጡም፡፡ ምክንያቱም የመማሪያ ክፍሉን ደንብ በቅድሚያ ካላስከበሩ ትምህርቱን በመደማመጥ ለማስኬድ እና ክፍሉን በስርዓት ለመምራት ያስቸግራቸዋል፡፡

የመማሪያ ክፍል የንግግር ልውውጥ በተቋሙ ደንብና ሥርዓት መሠረት በመምህሩ ፍቃድ የሚከናወን እንጂ ተሳታፊዎች እንደፈለጉ የሚሳተፉበት አይደለም፡፡ መስተጋብሩ የትምህርቱን ዓላማ በሚያሳካ መንገድ መከናወን እና መመራት አለበት፤ ተማሪዎቹም በእየተራ መናገር እና መደማመጥ አለባቸው፡፡ ስለሆነም መምህራን የመማሪያ ክፍሉን ደንብ ያስከብራሉ፤ የመናገር ተራውን ለሚፈልጉት ተማሪ ይሰጣሉ፡፡

በዚህ የተነሣም ተማሪዎች በሁሉን አቀፍ ውይይት ጊዜ የመናገር ተራው ይሰጣቸው ዘንድ እጃቸውን በማውጣት የመምህርቷን ፍቃድ በአክብሮት ይጠብቃሉ፡፡ ይህንም በተራ 169 ላይ መምህርቷ "ቆይ! እጃችሁን ዝም ብላችሁ አውጡ" በማለት ገልጸውታል፡፡ ስለዚህ መምህራን ይህን ማኅበራዊ ደንብ ለማስከበር እና የትምህርቱን ዓላማ ለማሳካት ይችሉ ዘንድ የማስተናበሪያ ዲስኩርን ይገለገላሉ፡፡ እንደዚህም ሆኖ አንዳንድ ጊዜ ተራ የተሰጠው ተማሪ ሐሳቡን ተናግሮ ሳይጨርስ ሌሎች ተማሪዎች ጣልቃ እየገቡ የንግግር ልውውጡን ደንብ በመጣስ ሐሳባቸውን ይገልጻሉ፡፡

ምሳሌ 5

| | | |
|---|---|---|
| 288 | መ፡ | ነፃ ምዕላዱ ^ |
| 289 | ተ13፡ | + ((በመማሪያ ደብተሩ ላይ የጻፈውን እየተመለከተ ዝም አለ)) |
| 290 | ተሀ፡ | -እኛ፣ -እኛ ((የመናገር ተራው ሳይፈቀድላቸው ተናገሩ)) |
| ---> 291 | መ፡ | እምጠይቀው እሱን እኮ ነው! ሥርዓት ያዙ! |
| 292 | ተ13፡ | ጥገኛ ምዕላዱ ^ |
| | መ፡ | እሀም |
| | ተ13፡ | -እኛ |

(ምዝግብ መረጃ መ፣ ክ3)

ከዚህ በላይ ከቀረበው መረጃ እንደሚስተዋለው፣ ተማሪው (ተ13) እና መምህሩ ነፃና ጥገኛ ምዕላድን በተመለከተ የሐሳብ ልውውጥ እያደረጉ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ተ13 ለተጠየቀው ጥያቄ መልሱን ተናግሮ ሳይጨርስ፣ ያልተጠየቁት ተማሪዎቹ ጣልቃ ገብተው (በ290ኛ የመናገር ተራ ላይ) ፍንጭ መስጠት ጀምረዋል፡፡ በዚህ ድርጊታቸውም የመምህሩን ሥልጣን እና የንግግር ልውውጡን ደንብ ተላልፈዋል፡፡

ስለሆነም መምህሩ "እምጠይቀው እሱን እኮ ነው! ሥርዓት ያዙ!" በማለት በ291ኛው የመናገር ተራ ላይ ተማሪዎቹ ከሥርዓት እየወጡ ያልተገባ ፍንጭ እየሰጡ መሆናቸውን አስገንዝበዋል፡፡ እንግዲህ በዚህ ትንታኔ መሠረት የማስተናበሪያ ዲስኩር ተማሪዎች የመማሪያ ክፍሉን ሥርዓትና ደንብ

ጠብቀው ይሰተፉ ዘንድ ሥርዓት አስይዞ ለመምራት በአገልግሎት ላይ ውሏል። የተቋማዊ ዲስኩር ትንተና እንደሚያስተምረው፣ ተሳታፊዎች በንግግር መስተጋብራቸው ጊዜ ሥራዬ ጉዳዬ ብለው በተቋሙ ዓላማ ላይ በእጅጉ ይጠመዳሉ። በመማሪያ ክፍል ዓውድም የመምህሩ እና የተማሪው ዲስኩር በትምህርቱ ዓላማ ላይ ያተኩራል፣ ይጠመዳል። በዚህን ጊዜ የመማር እና የማስተማር ዓላማው ግቡን እንዳይመታ የሚያደናቅፉ ጣልቃ ገብ ተግባራት ካሉ በፍጥነት ይወገዳሉ። ከዚህ አኳያ አደናቃፊ በሆነ ድርጊት ገብቶ የተገኘ ተማሪም ከድርጊቱ ይታቀብ ዘንድ ይገሠጻል፣ እንዳስፈላጊቱም ቅጣት ሊጣልበት ይችላል።

ምሳሌ 6

*82 መ: ... አንዳንድ ተማሪዎች ማስቲካ ስታላምጡ እያየኋችሁ ነው። ማስቲካ እሚላመጥበት "ክላስ" አይደለም። "ፕሊስ" አስወግዱ! እያየኋችሁ ስለሆነ ነው።*

(ምዝግብ መረጃ መ፣ ክ1)

ከዚህ በላይ በቀረበው ምሳሌ ከመምህሩ አንደበት እንደሚደመጠው፣ መምህሩ እያስተማሩ እያለ ጥቂት ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያውም በትምህርት ሰዓት "ማስቲካ" ሲያኝኩ አይተዋል። በእርግጥም የሌሎች ተሳታፊዎችን ትኩረት ሊሰርቅ ስለሚችል "ማስቲካ" ማኘክ በትምህርት ሰዓት የማይፈቀድ ድርጊት ነው። ስለሆነም መምህሩ "*ማስቲካ እሚላመጥበት ክላስ አይደለም*" ሲሉ ድርጊቱን የፈጸሙትን ተማሪዎች ገሥጸዋቸዋል። የዓረፍተንግግሩ አንድምታም፣ ይህ የትምህርት ሰዓት በትጋት የምትከታተሉት እንጂ በዋዘ ፈዛዘ የምታሳልፉት አይደለም የሚል ነው።

ተማሪዎቹ ከዓውዱ ጋር በማይሄድ እርባና ቢስ ድርጊት የሚጠመዱ ከሆነ የትምህርቱን ፍሬ ነገር ላይገነዘቡት ይችላሉ። እየቀረበ ያለውን ትምህርት በጥሞና እንዲከታተሉም፣ መምህራን አደናቃፊ ድርጊቶችን ለማስወገድ ጥረት ያደርጋሉ። ስለሆነም ተማሪዎቹ ከድርጊታቸው ይታቀቡ ዘንድ "ፕሊስ አስወግዱ!" ሲሉ መምህሩ በቁጣ አሳስበዋል።

እንግዲህ ከዚህ በላይ የቀረበው ትንታኔ እንደሚያመለክታው የማስተናበሪያ ዲስኩር የትምህርቱ ዓላማ ስኬታማ ይሆን ዘንድ የቀረበ ተግሣጽ ነው። ይሁን እንጂ ተማሪዎች የመማሪያ ክፍሉን ደንብ ሲጥሱ በተግሣጽ ብቻ አይታለፉም። ምናልባትም ጥፋታቸው አስነዋሪ ሆኖ ከተገኘ ቅጣት ሊጣልባቸው ይችላል።

ምሳሌ 7

| | | |
|---|---|---|
| 10 | መ: | ... ማን ነህ? አንተ! ተነሥ! ((የቀኝ እጅ መዳፉን ወደ ላይ ገልብጦ ይነሣ ዘንድ እየጠቀሰው)) |
| 11 | ተ2፡ | እኔ? |
| 12 | መ፡ | አዎ አንተ! |
| | ተ2፡+ | |
| | መ፡ | ተነሥ! ውጣ! ተነሥ ውጣልኝ! ((ወደ በሩ የኋሊት እየሄዱና ተከትሏቸው እንዲወጣ በፍጥነት ደጋግመው በእጃቸው እየጠቀሱት)) |
| | ተ2፡ | ((ተነሥቶ እንዳጎነበሰ በሩን ከፍቶ ወጣ))። |

(ምዝግብ መረጃ ረ፣ ክ1)

ከዚህ ዲስኩር መገንዘብ እንደሚቻለው፣ ተማሪው (ተ2) የመማሪያ ክፍሉን ሥርዓትና ደንብ የሚጥስ ተግባር ሲፈጽም መምህሩ ዓይተውታል። ይህን ድርጊቱን በተግሣጽ ሊምሩት አልፈለጉም። በድርጊቱ ክፉኛ ስለተበሳጩም "አንተ ተነሥ!" ሲሉ በቁጣ ድምፀት ተናግረዋል። ምናልባትም የተማሪው ጥፋት ምን እንደሆነ ለክፍሉ ተማሪዎች በይፋ ያልተገለጸው፣ በመምህሩ ዘንድ አስነዋሪ ሆኖ ስለተገኘ ሊሆን ይችላል። ለዚህም መምህሩ "... ተነሥ ውጣልኝ!" በማለት በተማሪው ላይ ቅጣት መወሰናቸውን ሳያመነቱ አሳውቀዋል። ወዲያውኑም ተማሪውን ከመማሪያ ክፍል በማስወጣት ቅጣቱን ተግባራዊ አድርገዋል።

ተማሪውም ቢሆን ቅጣቱን አምኖ የተቀበለ ይመስላል። ምክንያቱም ጥፋቱን ለማስተባበል ሳይሞክር ድምፁን አጥፍቶ ከመማሪያ ክፍሉ ወጥቷል። ምናልባትም ይህን ያደረገው በክፍል ጓደኞቹ ፊት ድርጊቱን ይፋ አውጥቶ ማስተባበል የበለጠ አሳፋሪ ሆኖበትም ሊሆን ይችላል። በዚህ ትንታኔ መሠረት፣ የማስተናበሪያ ዲስኩር በመማሪያ ክፍል ዓውድ ቅጣትንም ለማስተላለፍ ተግባራዊ ሲደረግ በተጨባጭ ተስተውሏል።

የማስተናበሪያ ዲስኩርን እንስፈለጊነቱ መምህራን ምክር ለመለገስም ይጠቀሙበታል። ለምሳሌ መምህሩ የሚከተለውን ምክር ለተማሪዎቹ ሲለግሱ ተስተውለዋል።

ምሳሌ 8

40 መ፡… አንደኛ … መቼ ነው ይህን ፍርሃታችሁን አስወግዳችሁ ከሰው ፊት ቁማችሁ እምትናገሩት? ይሄን የፍርሃት ችግራችሁን ማስወገድ አለባችሁ። … ሁለተኛ ልምምድ ስታደርጉ ከራሳችሁ መጀመሩ በጣም ጠቀሜታ ይኖረዋል። … እናንተ ያደረጋችሁትን ነገር ሌላ ሰው እሚያቅ የለም። ስለዚህ ምንም እሚላችሁ የለም። … ይህን አጋጣሚ ብትጠቀሙበት፣ ጥሩ ንግግር ለመናገር እንድትችሉ ይረዳችሁ ነበር።

(ምዝግብ መረጃ ረ፣ ክ1)

ከዚህ በላይ ከቀረበው ዲስኩር እንደሚስተዋለው፣ ተማሪዎቹ በጓደኞቻቸው ፊት ቆመው ንግግር ለማድረግ ፍርሃት እንዳደረባቸው መምህሩ ተገንዝበዋል። እንቅፋት ከሆኑባቸው ነገሮች አንዱ ፍርሃት እንደሆነም ለተማሪዎቹ ገልጸዋል። ለዚህም መፍትሔው በሚያውቋቸው ተማሪዎች መካከል ቆሞ የመናገር ልምምድ ማድረግ እንደሆነ ጠቁመዋቸዋል። ጥሩ ተናጋሪ መሆን የሚቻለው፣ ፍርሃትን አስወግዶ በመለማመድ እንደሆነ አስግንዝበዋቸዋል። ስለሆነም ለዚህ ዓላማ ተብሎ የተዘጋጀውን የልምምድ ጊዜ ሊጠቀሙበት እንደሚገባም "ይህን አጋጣሚ ብትጠቀሙበት፣ ጥሩ ንግግር ለመናገር እንድትችሉ ይረዳችሁ ነበር" በማለት አስረድተዋል። ከዚህ በቀር የአቃፊና ታቃፊነት መዋቅራዊ ቅጥ አንባር በወጥነት ሲከሠት አልተስተዋለም። ስለዚህ የማስተናበሪያ ዲስኩር ሁልጊዜም በአቃፊነት አልተከሰተም።

ምሳሌ 9

261 መ፡ ሁለተኛው ቤቶች ((ሌላውን ተተንታኝ ቃል እየተናገሩ))

ተ6፡ ((ቁጭ እንዳለች ለመናገር እየተዘጋጀች ሳለች))

---> 262 መ፡ተነሽና!

263 ተ6፡ ((ተነሣችና)) ነጻ ምዕላድ ቤት

መ፡ እህም

ተ6፡ ጥገኛ ምዕላድ -ዎች

264 ተህ፡ አይደለም! አይደለም። ((የመናገር ተራው ሳይፈቀድላቸው))

ተ6፡ ((ወደ ደብተሯ እየተመለከተች አፏን በግራ እጇ አፈነች))

(ምዝግብ መረጃ መ፣ ክ3)

ከዚህ በላይ ከቀረበው የጥያቄ እና መልስ የንግግር ልውውጥ እንደሚስተዋለው፣ መምህሩ በንግግር ልውውጡ 261ኛ ተራ ላይ የሚተነተን ቃል አቅርበዋል። ይህን ቃል እንድትተነትንም የመናገር ተራውን ለተማሪዋ (ተ6) ተፈቅዶላታል። ነገር ግን ተማሪዋ ከመቀመጫዋ ሳትነሣ ልትናገር ስትል "ተነሽና!" በማለት መምህሩ አስተናብረዋታል። በዚህ ሳቢያም ከመቀመጫዋ ተነሥታ ምላሽዋን ሰጥታለች።

እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ሌላው ቁምነገር የመምህሩ ማስተናበሪያ የተከሠተበት መዋቅራዊ ቦታ ነው። ማስተናበሪያው የተከሠተው በመምህሩና በተማሪዋ መካከል ሲካሄድ የነበረውን የማስተማሪያ ዲስኩር በማቋረጥ ጣልቃ ገብቶ ነው። በሌላ አገላለጽ፣ በማስተማሪያ ዲስኩር እቅፍ ውስጥ ገብቶ ተከሥቷል ማለት ነው።

ስለዚህ በዚህ ምሳሌ መሠረት የማስተናበሪያ ዲስኩር ሁልጊዜም የማስተማሪያ ዲስኩርን አቃፊ ሆኖ ይዋቀራል የሚለው ድምዳሜ አጠያያቂ ይሆናል። ምክንያቱም በዚህ መረጃ ላይ የተደረገው ትንታኔ የማስተናበሪያ ዲስኩር በማስተማሪያ ዲስኩር እቅፍ ውስጥ በጣልቃ ገብነት እንደሚዋቀር አመልክቷል።

## 4. ማብራሪያ

በመማሪያ ክፍል ዲስኩር ንድፈሐሳብ መሠረት፣ የመማሪያ ክፍል ዲስኩር የማስተ**ናበሪያ**ና የማስተ**ማሪያ** ዲስኩር በመባል በሁለት ይከፈላል። ይሁን እንጂ የሁለቱን ዲስኩሮች የአወቃቀር ሥርዓት ለመረዳት ተገቢ መረጃ መስበሰብ እና በተገቢ ዘዴ ትንታኔ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለሆነም በዚህ ጥናት የተነሣው የመጀመሪያው ጥያቄ "የማስተናበሪያ ዲስከር ከማስተማሪያ ዲሰስኩር ጋር ያለው መዋቅራዊ ቅንጅ ምን ይመስላል? የሚል ነበር።

በጥናቱ መነሻ ላይ እንደተገለጸው፣ የማስተማሪያ ዲስኩር በማስተናበሪያ ዲስኩር እቅፍ ውስጥ ይገኛል [8] የሚል ነበር። ነገር ግን በዚህ ጥናት የተደረገው ትንተና ውጤት እንደሚያሳየው የማሰተናበሪያ ዲስኩር ሁል ጊዜም ቢሆን ለማስተማሪያ ዲስኩር አቃፊ ሆኖ ይገኛል ከሚለው የ[8] ድምዳሜ ጋር የሚስማማ አይደለም። ምክንያቱም አቃፊ ሊሆን የሚችለው በርእሰጉዳዩ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ ሲገኝ እንጂ በርእሰጉዳዩ መካከል ሲከሠት አይደለም። በዚህ ጥናት ውጤት

መሠረት፣ በመካከል ሲከሰት ግን ታቃፊ እንጂ አቃፊ አልሆነም፡፡ በማስተማሪያ ዲስኩር መካከል ጣልቃ እየገባም አገልግሎት እንደሚሰጥ በተደረገው ትንታኔ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የመዋቀሩን ቅጥ አንበር የሚወስነው አግልግሎታዊ ፍላጎቱ ነው፡፡

ሆኖም ግን የ[8] አባባል ትክክል የሚሆነውና መዋቅሩም ሊከሠት የሚችለው፣ የአንድን ርእሰጉዳይ አጀማመርና አጨራረስ ለማመልከት በሚነገርበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ በቀር የአቃፊና ታቃፊነት መዋቅራዊ ቅንጅት በወጥነት ሊከሠት በዚህ ጥናት መረጃ ላይ አልተስተዋለም፡፡ ስለዚህ የማስተናበሪያ ዲስኩር ሁልጊዜም በአቃፊነት ሲከሠት አይችል፡፡ ምንም እንኳ ተጨማሪ ሌላ ጥናት ማድረግን የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ለልዩነቱ ምክንያት የሆነው፣ በዚህ ጥናት ውጤት መሠረት፣ የማስተማር ባህል እና የተግባቦት ፍላጎት መለያየት ሊሆን ይችላል፡፡

ሌላው የዚህ ጥናት መሠረታዊ ጥያቄ "የማተናበሪያ ዲስኩር በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለጊዜ ለምን ለምን አገልግሎት ይተገበራል?" የሚለው ነው፡፡ የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው፣ የማስተማሪያ ዲስኩር በማስተናበሪያ ዲስኩር እቅፍ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን እውቀትን ለማስረጽ፣ ክሂልን ለማዳበር እና አመለካከትን ለማሳደግ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ይህም የማስተማሪያ ዲስኩር ዕውቀትን ለማሥረጽና ክሂልን ለማበልጸግ ተግባራዊ የሚደረግ ነው ከሚለው የ[5] ግኝት ጋር ይደጋገፋል፡፡ እነ [12: 562]ም "ዕውቀት፣ ብቃትና ሳይንሳዊ ሂደት የማስተማር ዲስኩር ይዘቶች ናቸው" በማለት በጥናታቸው ቀደም ብለው አረጋግጠዋል፡፡

የማስተማሪያ ዲስኩር፣ ተማሪዎቹ ስለሚማሩት ቋንቋ ዕውቀትና ክሂል ያገኙ ዘንድ ትምህርቱ የሚሰጥበት ዘዴ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ግኝት፣ ትምህርታዊ ዲስኩር "በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመምህሩና በተማሪዎቹ መካከል የሚካሄደውን የመማርና የማስተማር ክንውን የሚያመለክት የዲስኩር ዓይነት ነው" ከሚለው የእነ [12፡ 67] ድምዳሜ ጋር ይሰናኛል፡፡

## 5. ማጠቃለያ

የተደረገው አጭር ትንታኔ እንደሚያመለክተው፣ የማስተናበሪያ ዲስኩር ትምህርቱ በተቀላጠፈ መልኩ ይካሄድ ዘንድ የማስተማሪያ ዲስኩርን ያግዛል፡፡ አደናቃፊ ድርጊቶችን በማስወገድ የመማርና የማስተማር ሂደቱ በተቀላጠፈ መንገድ ይካሄድ ዘንድ በተለያየ መልኩ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ ይህም የተማሪዎቹን ባህሪ ለማረም፣ ተሳትፏቸውን ሥርዓት ለማስያዝ፣ ምክር ለመለገስ፣ የተጀመረው ርእሰጉዳይ ተጠናቅቆ ሌላው ሊቀጥል መሆኑን ለማሳወቅ እና የመልመጃውን አከዋወን ለመግለጽ በሚደረገው የማስተማር ሂደት የማስተናበር ተግባራትን ለማከናውን አገልግሏል፡፡ እነዚህ ክንውኖች በተስተካከለ መንገድ ባይተገበሩ የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚከናወነው የማስተማሪያ ዲስኩር (ዕውቀትን፣ ክሂልን እና አመለካከትን የማሥረጽ ተግባር) ይስተጓጎላል፡፡ ስለዚህ የማስተናበሪያ ዲስኩር የመማር እና የማስተማር መስተጋብሩ ጥራቱ ተጠብቆ እንዲከናወን በማድረግ ረገድ የማይናቅ ሥነትምህርታዊ አስተዋጸዖ አድርጓል፡፡

## 6. መደምደሚያ

በዚህ ጥናት ግኝት መሠረት የማሰተናበሪያ ዲስኩር ሁልጊዜ ለማስተማሪያ ዲስኩር አቃፊ ሆኖ አይገኝም፡፡ ምክንያቱም አቃፊ ሊሆን የሚችለው በርእሰጉዳዩ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ ሲገባ ነው፡፡ ነገር ግን እንደተገልጋዩ ፍላጐት በማስተማሪ ዲስኩር መካከልም ጣልቃ በመግባት መከሰት ይችላል፡፡ በዚህን ጊዜ አቃፊቱ ቀርቶ የማስተማሪያ ዲስኩር ታቃፊ ይሆናል፡፡ የማስተማር ብቃትን በቋንቋ አጠቃቀም አማካኝነት ለማጥናት እና ተገቢ ሒስ ለማቅረብም፣ በቅድሚያ የማስተናበሪያ ዲስኩርን መመልከት እና ከዚያም የማስተማሪያ ዲስኩርን ማጤን ተገቢ እንደሆነ ጥናቱ አመልክቷል፡፡

### የጥቁምታ አስተያየት

ይህ ጥናት ቀደም ብሎ የነበረው ንድፈሐሳብ የነበረበትን ክፍተት በመጠቆም እና ክፍተቱ የሚሞላበትን ሒስ ለመጠቆመ ተሞክሯል፡፡ ከዚህም ባሻገር ይህ ጥናት በማስተናበሪያ እና በማስተማሪያ ዲስከሮች አወቃቀር እና አገልግሎት ላይ ያተኩር እንጂ በእነዚህ ዲስኩሮች ሳቢያ የሚከናወነውን የክፍል አመራር፣ የትምህርት አተገባበር፣ የምዘና አከዋወን እና የግብረመልስ አሰጣጥ ስልት በዝርዝር አልተመለከተም፡፡ ስለሆነም

በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ዲስኩር ትንተና ጥናት ቢሠራ፣ የመስተጋብሩን ጉድለት ነቅሶ ለማውጣት፣ ለማረም እና ገንቢ ሒስ ለማቅረብ ያስችላል፡፡ የማስተማር ሥራ በየጊዜው በሚደረግ ጥናት እየተሻሻለ፣ በእየዘመኑ በሚከሰቱ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴዎች እየታገዘ እና እየታደሰ ከትውልድ ወደ ትውል የሚሻጋገር ባህል ነው፡፡ ስለዚህ የመማሪያ ክፍል ዲስኩር ትንተና ሥነትምህርታዊ፣ መስተጋብራዊ እና ተግባቦታዊ ፋይዳ ላይ ያነጣጠረ አጭር ሥልጠና በሥራ ላይ ላሉት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቢሰጣቸው እና በመምህራን ሥልጠና ሥርዓተትምህርት ውስጥም በይዘትነት ቢካተት ለትምህርቱ ጥራት የተሻለ እገዛ ያደርጋል፡፡

## የማጣቀሻ ጽሑፎች


1. Meng, Xuemei, and Xuesong Wang: Action study of teacher's language on EFL classroom interaction. Theory and Practice in Language Studies, 2011, 1(1): 98-104.

2. Nomlomo V: Classroom interaction: Turn-taking as a pedagogical strategy. Per Linguam: a Journal of Language Learning= Per Linguam: Tydskrif vir Taalaanleer. 2010, 26(2):50-66.

3. Willis, J: "Spoken discourse in the ELT classroom: a system of analysis and a description." PhD diss., University of Birmingham, 1981.

[4] Rymes, B: Classroom discourse analysis: A tool for critical reflection. Cresskill: Hompton. 2008.

[5] Bernstein B. The Structure of Pedagogic Discourse: Class Codes. 1990.

6. Christie F. Pedagogic discourse in the primary school. Linguistics and education. 1995, 7(3):221-42.

7. Christie F. Classroom discourse analysis: A functional perspective. Bloomsbury Publishing; 2005.

8. Temple, C. Teaching and learning mathematics discourse in Romania classroom: A critical discourse analysis. Unpublished doctoral dissertation, Syracuse University, 2008.

9. Mustaffa R, Aman I, Saupi ND, Noor NM: Interdiscursivity of pedagogic discourse in the ESL classroom in primary school. e-BANGI. 2014,9(1):63.

10. Basil B: Vertical and horizontal discourse: an essay. British Journal of Sociology of Education. 1999; 20(2):157-73.

11. Jenks C: Language speaks more than it says: some reflections on the work of Basil Bernstein. British Journal of Sociology. 2010, 2: 61.

12. Morais AM: Basil Bernstein at the micro level of the classroom. British journal of sociology of education. 2002, 23(4):559-69.

13. Jefferson G: A note on laughter in 'male–female'interaction. Discourse Studies. 2004, 6(1):117-33.

14. Sacks H, Schegloff EA: Jefferson G. A simplest systematics for the organization of turn-taking for conversation. Language. 1974, 50(4):696-735.

15. Tannen D: Analyzing discourse: Text and talk. Washington: Georgetown University, 1982.

[16] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፡፡ አማርኛ መዝገበ ቃላት፡፡ አዲስ አበባ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤1993፡፡

17. በላይ መኮነን፡፡ ሕያው ልሳን፡፡ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፤1999፡፡

18. ከበደ ይመር፡፡ ‹‹የአማርኛ ትምህርት ክፍለጊዜያት የመምህር እና ተማሪ የንግግር ልውውጥ ትንተና፡፡” አማርኛ

በማስተማር ሥነዘዴ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ያልታተመ፣ 2000።

19. ከበደ ይመር። ‹‹የመማሪያ ክፍል የድርድር ዲስኩር መንስኤ፣ ብልሃትና መፍትሄ ትንተና።›› በተግባራዊ ሥነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ያልታተመ፣ 2009።

20. አንዱዓለም ከበደ። “በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተግባቦት የአማርኛ ግብረንግግር ዓይነቶች፣ ቅጣምባር እና ተግባር ትንተና።” በተግባራዊ ሥነልሳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ማስተማር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ያልታተመ፣ 2016።